# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 237 ህዳር 20 2005 ገጽ 1


አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ህወአት/ወያኔ ውብ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ መታሰቢያ ቅርሶቻችንን ከኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ጋር የተያያዙ ናቸዉ ያላቸዉን ቦታዎች ሁሉ ከኢትዮጵያ ካርታ ላይ እየፋቀ የአምባገነኑን የመለስ ፎቶ፤ የአባ ጳዉሎስ ሀዉልትና የከሀዲ ጀኔራሎችን ምስል እያስቀመጠ ነዉ። በአጠቃላይ የወያኔ ዘረኞች እዉነተኛዉን የኢትዮጵያ ታሪክ በእነሱ የዉሸትና የፈጠራ ታሪክ እየተኩ ነዉ።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-

## የወያኔ የይስሙላ ፓርላማ ህገመንግስቱ ዉስጥ ያልተጻፈ ሹመት አጸደቀ

ሀ/ማሪያም ደሳለኝ ለረጂም ግዜ ሲጠበቅ የነበረዉን የዉጭ ጉዳይ ሚኒስተርነቱን ቦታ ጨምሮ ለሌሎች ሁለት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሮችና ለአንድ ሚኒስትር የሰጠዉን ሹመት ህዳር 20 ቀን 2005 ዓም የተሰየመዉ የወያኔ የይስሙላ ፓርላማ ያጸደቀዉ መሆኑን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ የግንቦት ሰባት ምንጮች ገለጹ። በዚህ ብዙ ኢትዮጵያዉያንን ባስገረመዉ ሹመት ህወሀት እንደተጠበቀዉ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትርነቱን ቦታ የወሰደ ሲሆን የኦህዴዱ ሙክታር ከድር በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የመልካም አስተዳደርና ሪፎርም ክላስተር አስተባባሪና የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትር ሆኖ ሲሾም የህወሀቱ ደብረ ፅዮን ገብረ ሚካኤል ደግሞ በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ማዕረግ የፋይናንስና ኢኮኖሚ ክላስተር አስተባባሪና የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ሆኖ ተሹሟል። ዶ/ር ደብረ ፅዮንና ሙክታር ከድር ከተደራራቢ ሹመቶች በተጨማሪ ምክትል ጠ/ሚኒስትር ሆነዉ ቢሾሙም ብዙዎችን ያስገረመዉ ላለፉት ሦስት ወራት ተጠባባቂ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ብዙ ስራዎችን በሰራዉና የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ ይሾማል ተብሎ ሲጠበቅ በነበረዉ በብርሀነ ገ/ክርስቶስ ቦታ ያልተጠበቀዉ ቴዎድሮስ አድሀኖም የዉጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ መሾሙ ነዉ።

የወያኔን የዉስጥ አሰራር በቅርብ ከሚያዉቁ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች በተገኘዉ መረጃ መሠረት ሙክታር ከድር በምክትል ጠ/ሚኒስትርነት ማዕረግ የመልካም አስተዳደርና ሪፎርም ክላስተር አስተባባሪ ሆኖ የተሾመዉ በኦህዴድ ዉስጥ የተፈጠረዉን ከፍተኛ ዉጥረት ለማርገብና ትላልቆቹን የኦህዴድ ባለስልጣኖች ለመደለል ነዉ እንጂ ወያኔ ከመልካም አስተዳደር ጋር የማይተዋወቅ አገዛዝ መሆኑ ብቻ ሳይሆን (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## ከ500 በላይ የአየር መንገድ የጉልበት ሰራተኞች የአህአዴግ ፎረም አባል አይደላችሁም ተብለዉ ከስራቸዉ ተባረሩ

በኢትዮጵያ አየር መንገድ ዉስጥ ተቀጥረዉ ለረጂም ግዜ የሰሩ የአየር መንገዱ የጉልበት ሰራተኞች የገዢዉ ፓርቲ የኢህአዴግ ፎረም አባል አይደላችሁም ተብለዉ ከስራቸዉ እንደተባረሩ አንድ ስማቸው እንዳይገለጥ የፈለጉ የአየር መንገድ ሰራተኛ ለኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ስልክ ደዉለዉ አጋለጡ።

እነዚህ ቁጥራቸዉ ከ500 እስከ 700 የሚደርስ ሠራተኞች አየር መንገዱን ከአራት አመት በላይ ያገለገሉ ሲሆን አሁን ግን ዜግነታቸዉ ተረስቶ የኢህአዴግ ፎርም አባል አይደላችሁም የሚል ህግወጥና ሰንካላ ምክንያት እየተሰጣቸዉ ስራቸዉን እንዲለቅቁና በምትካቸዉ በስልጠና ላይ የሚገኙ የኢህአዴግ ፎረም አባላት የሆኑ ወጣቶች እንደሚተኳቸዉ ለማወቅ ተችሏል። ከዚህ በተጨማሪ ከስራ የተባረሩት ሰራተኞች የኢህአዴግ ፎረም አባል ከሆኑ ወደስራቸዉ እንደሚመለሱ የተነገራቸዉ ሲሆን ይህ አድሎ የሞላበት አሰራር ወያኔ በቅርቡ የሚደረገዉን የወረዳና የከተማ ምርጫ እንደለመደዉ 99.6 በመቶ አሸነፍኩ ለማለት የሚሰራዉ የተንኮል ዘመቻ ከመሆን ሌላ ምንም ትርጉም የሚሰጠዉ አይደመለም ሲል አንድ ከስራዉ የተባረረ ወጣት በቁጣ ስሜቱን ገልጿል።

## ህወሀት ዉስጥ በተፈጠረዉ አለመግባባት የተነሳ ስራዉን ተቀምቶ የነበረዉ ጄኔራል ሞላ ወደ ስራዉ ተመለሰ

የዘረኛስውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ ከዚህ አለም በሞት መለየት ለህዝብ ከመገለጹ በፊት በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ሲካሄድ የቆየውን ግምገማ ተከትሎ ከአየር ሀይል አዛዥነት ቦታዉ ተነጥቆ የነበረዉ ሜጀር ጄኔራል ሞላ ሀይለማሪያም የቀድሞ ቦታዉን እንደገና መልሶ መያዙን መከላከያ ሚኒስቴር ዉስጥ የሚገኙ ምንጮቻችንን በመግለጽ የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ በላከልን ዘገባ አመለከተ።

የመለስ ዜናዊ በጠና መታመም ከተሰማ በኋላ እንደማይተማመን ኋደኛ በየቀኑ የሚሰበሰቡት የህወሀት አባላት በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ተከታታይ ስብሰባዎችን ያካሄዱ ቢሆንም አንዱ ሌላዉን በፍጹም ስለማያምን ይህ ነዉ ተብሎ የሚጠቀስ ዉሳኔ ሳያሳልፉ የስብሰባ ግዜያቸዉን በተራ ጭቅጭቅ አሳልፈዋል።

(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## ሀይለማርያም ደሳለኝ የራሱን ካቢኔ እንደማያዋቅር ተነገረ

የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ወደ ይስሙላ ጠቅላይ ሚንስትርነት የመጣው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በይስሙላ ከተካበት ግዜ ጀምሮ ከዛሬ ነገ የራሱን ካቢኔ ይመስርታል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ ከአሁን በኋላ ሌላ ምርጫ እስኪደረግ ድረስ አዲስ ካቢኔ እንደማይመሰርት ለወያኔ ኢህአዴግ ማሳወቁን ለዝግጇት ክፍላችን ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቆሙ:: አንደ ምንጮቹ አባባል ኃ/ማሪያም ደሰለኝ የራሱን ካቢኔ ማዋቀር ያልቻለዉ በይስሙላ ምርጫም ቢሆን አሸንፎ የመጣ አዲስ ጠ/ሚኒስትር ባለመሆኑ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏ። ኃለማርያም ደሳለኝ በመለስ ዜናዊ እግር የተተካ በመሆኑ አዲስ ካቢኔ ለፓርላማ አቅርቦ ማስጸደቅ አንደማይችል ቢነገርም እንደዚህ አይነቱን አሰራር በተመለከተ ህገመንግስቱ ላይ የተቀመጠ ምንም ነገር ስለሌለ ኃ/ማሪያም ደሰለኝ ካቢኔ ማቋቋም አይችልም የሚለዉ ህግ ህዝቡን በየቦታዉ ማወያየት ጀምሯል።

ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ በቆየባቸዉ ባለፉት ሦስት ወራት ለፓርላማዉ አቅርቦ ያስሾመዉ ሁለት ባለስልጣኖችን ብቻ ሲሆን አነሱም ምክትል ጠቅላይ ሚኒሰትር ሆኖ የተሾመዉ የትምህርት ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንንና ተጠባባቂ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመዉ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁነዲን ሳዶ ባለቤቱ በሽብርተኝነት በመከሰሷና እሱን በተመለከተ ኦህዴድ ዉስጥ በተካሄደ ግምገማ የተነሳ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትርነቱ ይነሳል ተብሎ እየተጠበቀ ቢሆንም መቼ ይነሳል ማንስ ይተካዋል የሚሉት ጥያቄዎች ግን አስካሁን ድረስ መልስ የተገኘላቸዉ አይመስልም።

## ግፈኛው የወያኔ አገዛዝ በመላ አገሪቱ ሙስሊሞችን እያስገደደ ለተቃውሞ ሰልፍ ሊያስወጣ መሆኑ ተሰማ

ከወያኔ ኢህአዴግ የተገኙ ምንጮችን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደገለጸው በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙና ዘረኛው አገዛዝ በሙስሊሙ ላይ በሚፈጽመው ኢሰብአዊ ድርጊት የተነሳ ተቃውሞ ያስነሳሉ በተባሉ አካባቢዎች በሙሉ ፣ የአገዛዙን አቋም የሚደግፉ አስገዳጅ ሰልፎች እንደሚደረጉ ታውቋል።

አብዛኛው ሙስሊም ህዝብ ተገዶ እንዲወጣ፣ የወያኔ ኢሃዴግ ድርጅት አባላት ከፍተኛ ተልእኮ እንደተሰጣቸው ለማወቅ ተችሎአል። በትናንትናው እለትም በቅርቡ የመንግስት ታጣቂዎች 4 ሰዎችን በገደሉበት ገርባ እና ደጋን ወያኔን የሚደግፉ አስገዳጅ ሰልፎች መደረጋቸውን ኢሳት አክሎ ገልጿል።
የሰልፉ ዋና አላማ በፍርድ ሂደት ላይ የሚገኙት የድምጻችን ይሰማ የሙስሊም ኮሚቴ አባላት አሸባሪዎች ናቸው የሚል መልእክት ለማስተላለፍ እንደሆነም የተገኘው መረጃ ያመለክታል ብሏል ኢሳት። ወያኔ ኢህአዴግ በኮሚቴ አባላቱ ላይ ለፍርድ ቤቱ ጠንካራ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ በዳኞች ላይ ተጽኖ ለመፍጠር ማሰቡን የደረሰን መረጃ ያመለክታል ሲል ኢሳት ዘገባውን አጠቃሏል።

## ዘረኛዉ የወያኔ ዘገዛዝ የአዲስ አበባን 125ኛ አመት እራሱን በማሞካሸት አከበረ

ላለፈው አንድ ዓመት በተለያዩ ቦታዎች የራሱን ዝናና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ በሞት የተሰናበተ መሪዉን በደም የጨቀየ ታሪክ ሲተርክ የኖረው የወያኔ አገዛዝ የአዲስ አበባ ከተማ 125ኛ ዓመት የምሥረታ ክብረ በዓል በሚል ባለፈዉ ቅዳሜ ኅዳር 15 ቀን 2005 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ስታዲየም በተመሳሳይ ሁኔታ ተከብሮ መጠናቀቁን አዲስ አበባ ዉስጥ የሚገኙ ምንጮቻችን በላኩልን ዜና ገለጹ:: የአዲስ አበባ ከተማ የልደት በአል የተከበረዉ ይህችን የኢትዮጵያና አፍሪካ መዲና የቆረቆሯትና “አዲስ አበባ” የሚል ዉብ ስም የሰጧት የእቴጌ ጣይቱና የአፄ ምኒልክ ስም አንድም ግዜ ሳይጠቀስ እንድያዉም የወያኔ ዘረኞች የዉሸት ገድል እየተነገረና ከተማዋ በመለስ ዜናዊ ፎቶ ተከብባ መሆኑን ዘጋቢዎቻችን አክለዉ የላኩልን ዜና ያስረዳል። ለኢትዮጵያና ለታሪኳ ከፍተኛ ጥላቻ ያላቸዉ የወያኔ መሪዎች አድዋ ላይ ጋሻ አንስተው ከቅኝ ገዢዎች ቀንበር ያዳኑንን የታላቁን መሪ የዳግማዊ ምኒልክንና የባለቤታቸዉን የእቴጌ ጣይቱን ስም ለምልክት አንኳን ሳይጠቅሱ እነዚህ ሁለት ኢትዮጵያዉያን ጀግኖች የቆረቆሯትን ከተማ 125ኛ የልደት በአል ማክበሩ የኢትዮጵያን ህዝብ እጅግ በጣም ያሳዘነ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል።

በአዲስ አበባ ስታድዮም በተካሄደዉ የበአሉ መዝጊያ ፕሮግራም ላይ ንግግር ያደረገዉ የወያኔዉ ተላላኪ ኩማ ደመቅሳ አዲስ አበባ በነገስታቱና በደርግ ዘመን ልማትና ዕድገት ያልነበራት፣ ነዋሪዎቿ የትምህርት፣ የጤና፣ የመብራትና የንፁህ ውኃ አቅርቦትና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች አጥተው በድህነት የሚማቅቁባት ከተማ ነበረች ብሏል። የአዲስ አበባን ልደት (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔ ታሪክን የማፍረስ ዘመቻውን ቀጥሏል!!

ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ገና ከጫካ ሳይወጣ በስትራቴጂ ደረጃ የነደፈዉን ኢትዮጵያንና ታሪኳን የማጥፋት ዘመቻውን አሁንም እንደቀጠለ ነው። የወያኔ ዘረኞች የኢትዮጵያ ህዝብ የትግልና የመስዋዕትነት ምልክት የሆኑትን ጅግኖች ታሪክና የወያኔ አስራ ሰባት አመት የጫካ ትግል አሻራ ያላረፈባቸዉን ሰማዕታቶቻችንን የገድል ታሪክና ሀዉልት እያጠፉ በምትኩ የኔ ናቸዉ የሚላቸዉን የእነ አባ ጳውሎስን ዝከረ ሀውልትና የእነ መለስ ዜናዊን ምስሎች ብቻ በመዲናችን በአዲስ አበባ በማስቀረት፤ አዲስ አበባን የህዝብ ሳይሆን የወያኔ ታሪክ ማስታወሻ እያደረጋት ነዉ። ወያኔ በላፈዉ አመት አጋማሽ ላይ በልማት ስም በታሪካዊዉ ዋልድባ ገዳም ላይ የጀመረዉን የአገር ታሪክና ቅርስ የማጥፋት ዘመቻ አሁን ደግሞ የኢትዮጵያ ህዝብ አልበገረም ባይነት ታሪክ ተምሳሌት የሆኑትን የሰማዕቱን የአቡነ ጴጥሮስን ሀዉልት የባቡር ሀዲድ እሰራለሁ በሚል ሰበብ ለማፍረስ በዝግጅት ላይ ነዉ። ይህ የወያኔ የጥፋት ዘመቻ ደግሞ እኛ ካላቆምነዉ በቀር የማንነታችን መገኛ አረአያ የሆኑትንና የአበውን ጀግንነት፤ አልበገርም ባይነትና እምቢተኝነት የሚስታውሱን ግዙፍ የታሪክ ማስታወሻዎቻችን የወያኔ ቡልዶዘሮች ሰለባ የሚሆኑበት ቀን ሩቅ አይደለም። ይህን ዘረኛ አገዛዝ በቶሎ ማሰወገድ አለብን ሰንል ግባችን እድገትና ዲሞክራሲ ብቻ ሳይሆን በወያኔ እየላላ ያለዉን አንድነታችንን ማጥበቅና ወያኔ በየቀኑ እያወደመ ያለዉን የታሪክ ቅርሶቻችንን በፍጥነት ማዳንና መጠበቅ ጭምር ነዉ።

የጣሊያን ፋሺስቶች አቡነ ጴጥሮስን "አርበኞች የህዝብና የአገር ጠላት" ናቸዉ ብለዉ የሚያስተምሩ ከሆነ ዛሬዉኑ ከእስር ይፈታሉ ሲሏቸዉ አምላኬ ይህንን አላስተማረኝም ብለዉ የኢትዮጵያ ህዝብ ጠላቶች እነዚህ ፊት ለፊታችን የቆሙትና ከሩቅ አገር የመጡት ፋሺስቶች ናቸዉና የኢትዮጵያ ህዝብና መሬት ከእነዚህ ሀገር ቀሚዎች ስጦታ እንዳይቀበል" ብለዉ በህዝብ ፊት በጥይት ተደብድበዉ የሞቱ ጅግና ናቸዉ። ወያኔ የእኚህን ጀግና ሰዉ ታሪክ ሰበብ እየፈጠረ የሚያፈርሰዉ እንደም የእሱ አሻራ ስላላረፈበት በሌላ በኩል ደግሞ ህዝብ ይህንን ሀዉልት በተመለከተ ቁጥር የሚማረዉ አልበገርም ባይነትንና አልገዛም የሚል እምቢተኝነትን ስለሆነ ነዉ። ለዚህ ነዉ ወያኔ እንኳን በቁም ላሉት ሞተዉ ላንቀላፉት ጀግኖቻችንም የማይተኛዉ። ወያኔን የመሰለ አገር በቀል ወራሪ ሀይልን ለአንዴና ለመጨረሻ እናጥፋ ሰንል እንደዚህ አይነቱን በማንነታችንና በታሪካችን ላይ የሚፈጸመዉን በደል ስር ከመስደዱና ትውልድን ከማጥፋቱ በፊት ለማስቆም ነዉ።

ወያኔ በተለመደ ቅጥፈቱ ሀውልቱ ተመልሶ ይመጣል እያለ የሚናገረው ህዝብን ለማዘናጋት እንጂ ከቶዉንም እውነቱን አይደለም፤ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ እንደዚህ አይነቱን አይን ያወጣ ቅጥፍት ሃያ አንድ አመት ሙሉ አይቷል። ስለዚህ የኢትዮጵያ ህዝብ ይህንን ቅጥፈታቸውን ተረድቶ በምንም ነገር ሳይታለል አባቶቹ አስቀምጠውለት የሄዱትን የታሪክ አሻራዎች የመጠበቅ ግዴታ አለበት። የነጻነት ታሪክ አሻራና ቅርስን እያፈረሱ የሚሰሩት ልማት ከቶ ጥፋት እንጂ ልማት አይደለም። ትላልቅና እጅግ ዉስብስብ ለሆኑ ችግሮች መፍትሄ ያለዉ የምህንድስና ሙያ አዲስ አበባን ያክል ትልቅ ከተማ ዉስጥ አንድ ሳይሆን በብዙ ሺ የሚቆጠሩ መንገዶችንና የባቡር ሀዲዶችን የታሪክ ቅርሶቻችንን በማይነካ መንግድ እንዲሰሩ ማድረግ ይችላል። የአቡነ ጴጥሮስ ሀዉልት የቆመዉ አቡኑ ያንን ታሪካዊ ንግግር ባደረጉበትና ፋሽስቶች በጥይት በደበደቧቸዉ ቦታ ላይ ነዉና የኢትዮጵያ ህዝብ በእሳቸዉ ሀዉልት ላይ የተነጣጠረዉን የወያኔ ጠመንጃ ማክሸፍ ግዴታ አለበት።

ህወአት/ወያኔ ውብ ታሪካዊ ቦታዎችን፣ መታሰቢያ ቅርሶቻችንን ከኢትዮጵያ ህዝብ ታሪክ ጋር የተያያዙ ናቸዉ ያላቸዉን ቦታዎች ሁሉ ከኢትዮጵያ ካርታ ላይ እየፋቀ የአምባገነኑን የመለስ ፎቶ፤ የአባ ጳዉሎስ ሀዉልትና የከሀዲ ጀኔራሎችን ምስል እያስቀመጠ ነዉ። በአጠቃላይ የወያኔ ዘረኞች እዉነተኛዉን የኢትዮጵያ ታሪክ በእነሱ የዉሸትና የፈጠራ ታሪክ እየተኩ ነዉ። ይህ የጥፋት ዘመቻቸዉ ስር ከሰደደና መጪዉን ትዉልድ በዚህ ጥፋታቸዉ እየበከሉ የሚያሰተምሩ ከሆነ ጥፋቱን ማረም እጅግ በጣም ይከብዳልና የኢትዮጵያ ህዝብ ነገ ዛሬ ሳይል ወያኔ በያዘው የጥፋት ዘመቻ ላይ ሆ! ብሎ በመዝመት ታሪካችንን ና ሀገራችንን ከወያኔ አምባገነኖች መንጋጋ ማስለቀቅ ወቅቱ የሚፈልገው ግድ ነው። ይህን ባለማድረጋችን ደግሞ የታሪክ ተጠያቂዎች ያደርገናል።

በመጨረሻም ወያኔዎች ሊረዱት የሚገባቸዉ አንድ ሀቅ ቢኖር ግዜና ትውልድ እንደሚፋረደቸውና የጀግናውና የታጋዩ አቡነ ጴጥሮስ ሀውልት በማፍረስ ሀውልቱን እንጂ እሳቸዉ የተሰዉለትንትን አላማ ከቶ ሊያፈርሱት እንደማይችሉ ነው። ይህ የሚያሳየን ገድለ-ታሪክ ታሪክን አምጦ ወልዶ በእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ልብ ውስጥ በጀግነነት ገድል ተጽፎ፣ ተቀልሞና ተከትቦ መቀመጡን ነው፤ ከዚህ በተጨማሪ ወያኔዎች ኢትዮጵያ ዉስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው አፍሪካ ለዘላለም ሲከበር የሚኖርን ትልቅ የጀግንነት ስራ፤ ሀውልትን በማፍረስ ማጥፋት አንደማይችሉ ሊረዱ ያገባል እንላለን። ይልቁኑ ሃውልቱን ለማጥፋት የሚቆፈረው ጉድጓድ የወያኔ ማንነት የመጨረሻ መቀበሪያ የሚሆንበት ግዜ ሩቅ አለመሆኑን እያንድንዱ የወያኔ አባልና ደጋፊ አበክሮ ሊገነዘበዉ ይገባል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

## ኢቲቪ አሸባሪ !!! ኢቲቪ ሌባ !!! (*ህዝብ*)

ኢቲቪ አሸባሪ !!! ኢቲቪ ሌባ !!! ያለው ህዝብ ነው። ህወሃቶች ግን ይህን ያለው ህዝብ ሳይሆን አሸባሪ ነው ብለዋል።ህዝብን ከማያውቅ ዘረኛ ቡድን ከዚህ ውጪ ሌላ የሚጠብቅ ካለ ሞኝ ነው።

በተለያየ አጋጣሚ ኢቲቭ ሌባ፤ኢቲቭ አሸባሪ ተብሎ ተሰደቧል። ሚሊዮናት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ድምጻቸውን ከፍ አድርገው ኢቲቪ አሸባሪ ነው ! ኢቲቪ ሌባ ነው ! ብለዋል። ህወሃት እስካለ ድረስ ኢቲቪ "ሌባ እና አሸባሪ" እንደተባለ ይቆያል። ይህ ኢቲቪ የመናገር እንጂ የመስማት ተፈጥሮውን ያጣ በመሆኑ የህዝቡን ድምጽ አይሰማም። እንዲያውም ይሄው ኢቲቪ ተመልሶ የሚሊዮናትን ድምጽ *"የጥቂት አሸባሪዎች ድምጽ"* ሲል በድፍረት ተናግሯል። እንዲህ ብዙሃኑን ህዝብ በአደባባይ "አሸባሪ" ብሎ መሳደብ ለህወሃቶች ሥራም ጀግንነትም ነው። ግዜ የሰጠው ድንጋይ ቅል ይሰብራል እንደሚባለው ሆነና ጥቂት ነውረኛ ዘረኞች ብዙሃኑን ተጭነው በህዝብ ሃብት ህዝብን አሸባሪ እያሉ የሚያሰቃዩበት ሁኔታ ውስጥ እንገኛለን።

ኢቲቭ የህዝብ ጆሮና ዓይን መሆኑን ትቶ ዜጎችን ማዋረጃ እና ማጥቂያ መሣሪያ እንዲሆን የተደረገው ከዘረኝነት በቀር የሰለጠነ ፖለቲካን በማያውቁ ህወሃቶች እጅ በመውደቁ ነው። ህወሃቶች ከውልደታቸው ዘመን ጀምረው ህዝብን ከማሸበርና ከማሸማቀቅ በቀር ሌላ እውቀት ያላቸው አይደሉም።የአሜሪካን መንግስትም ከአሸባሪ ቡድኖች እንደ አንዱ አድርጎ መዝግቧቸው እንደነበረ መዛግብቶች ያመለክታሉ።አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ አሸባሪው የኢትዮጵያ ቴሌቭዥን ሳይሆን ከኢቲቭ ጀርባ ሳይፈለጉ የተንጠላጠሉ የኢትዮጵያ እና የህዝቧ ጠላቶች የሆኑት ህወሃቶች ናቸው። ህወሃት የህዝብ እና የአገር ጠላት ነው ሲባል አንዱ መገለጫው ይሄው ነው። ህዝቡን ሊጠብቅ ይገባው የነበረውን መገናኛ ብዙሃን ህዝቡን ለማጥቂያነት እንዲውል ማድረጋቸው።

ኢቲቪ አሸባሪ፤ ኢቲቪ ሌባ ሲል ከአጽናፍ እስከ አጽናፍ የተደመጠው ያ ድምጽ የታላቅ የህዝብ ድምጽ ነው። ህወሃት ሠላማዊ የህዝብ ድምጽን የመስማት ልማድ ያለው ድርጅት ባለመሆኑ የህዝቡን ድምጽ የአሸባሪ ድምጽ ብሎታል። የህወሃት ታሪክ የህዝብን ድምጽ ማፈን እንጂ የህዝብን ጥያቄ አድምጦ መብትሄ መፈለግ አይደለም። ይህን ሠላማዊ ድምጽ ***"የአሸባሪ ድምጽ ነው፤ ትዕግስቴም ተሟጧል"*** ብሎ መዛቱ ደግሞ አጥፊቼያችሁ እጠፋለሁ ከሚል ከንቱ ትዕቢት የሚመነጭ እንጂ ከሌላ ከየትም የሚመጣ አይደለም። ዛሬ የሚሊዮን ሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ህገ መንግስታዊ ጥያቄ ለመመለስ እምቢ ያለ ይሄ ዘረኛ ቡድን ነገ የየትኛውንም ቡድን ጥያቄ ለመመለስ ፈቃደኛ እንደማይሆን ከዚህ ድርጊቱ መረዳት ይቻላል።ህወሃት የህዝብን ጥያቄ መስማት ተፈጥሮው አለመሆኑን የኢትዮጵያ ሙስሊሞች ሠላማዊ እና ህጋዊ ጥያቄ ህያው ምስክር ሆኖ ይናገራል።

የተከበራችሁ ወገኖቻችን !

ህወሃት የሚመኘው እርሱ ብቻ ያለው ሁኖ፤እርሱ ጠግኖ እርሱ አፍርሶ ሌላው ሁሉ ህወሃት ፍረስ ሲለው ፈርሶ፤ ሂድ ሲለው ሂዶ ና ሲለው መጥቶ የተሠመረለትን ቀይ መስመር ሳያልፍ ከሙታን ትንሽ ከፍ ከህያዋን ግን ዝቅ ብሎ እንዲኖር ነው። የህወሃት የደስታውም ምንጭ የዜጎች ስቃይና መከራ እንጂ የዜጎች ምቾትና ድሎት አይደለም። ይሄ ዘረኛ ድርጅት እኔ ያልኩት ካልሆነ ብሎ ኢትዮጵያዊያንን ለብዙ መከራ ዳርጓል። ከግለሰቦች አልፎ ሂዶ ታላላቅ የሃይማኖት ድርጅቶችን ለማዳካም ያልማሰው ጉድጓድ የለም።በዚህ ከፉ ድርጊታቸውም ኦሮቶዶክስ ቤተክርስትያን ለሦስት እንድትከፈል ምክንያት መሆናቸው የሚረሳ አይደለም። አሁን ደግሞ አንድነቱን ጠብቆ ለብዙ ዘመን የኖረው ሙስሊም ማህበረሰብ እንዴት ሳይከፋፈል በሠላም ኖረ ብለው አብዛኛውን ሙስሊም ከአልቃይዳ እኩል አሸባሪ፤በምናምን ተደልለው ዲናቸውን የሸጡላቸውን ደግሞ ጥሩ ሙስሊም ብለው የተለመደውን መርዛቸውን በሙስሊሞች መካከል እየረጩ ነው።ይሄ አሳዛኝ ነው።

እናንተ ***"የትግራይ ነፃ አውጪ ነን*** "ብላችሁ ራሳችሁን በራሳችሁ የሾማችሁ ግብዞች ሆይ አድምጡ !!!

ምንም እንኳ የህዝብ ድምጽ መስማት ተፈጥሯችሁ ባይሆንም የሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ድምጽ ለመስማት እምቢ ማለት ግን እንደማይበጃችሁ ልንነግራችሁ እንወዳለን። ምንም እንኳ ከአሁን ተሻግራችሁ ነገን ለማየት የተጋረዳችሁበት የዘረኝነት መጋረጃ የማይፈቅድላችሁ (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በደል ይረሳል ወይስ ይለመዳል!

በደል የረሳል ወይስ ይለመዳል ወገን?

አንዳንዶች ሀገራቸውንና ህዝባቸውን ለማገልገል እድሜ ዘመናቸውን እንደጣሩ፣ እንደፈለጉ፣ እንደናፈቁ ሳይሳካላቸው ያልፋሉ። በሌላ በኩል ደግሞ ሌሎች ይህ ወረቃማ እድል ያለጊዜው እጃቸው ላይ ወድቆላቸው ያላግባብ ያለምንም ጥቅም ሲያሳልፉትና የወገንና የታሪክ ተጠያቂ ሲሆኑ እንመለከታለን። ከዚህም እጅግ በከፋ መልኩ ያገኙትን ሀገርንና ወገንን የመርዳት ወርቃማ እድል በተቃራኒው የሀገርን ሉአላዊነት ማስደፈሪያ፣ ወገንን ማስገረፊያ፣ ማሰቃያና ማሳደጃያ እንዲሁም ለራስ ምስል ግንባታ ብቻ በማዋል የሀገርም፣ የወገንም እንዲሁም የታሪክም ፍጹም ማፈሪያ ሆነው ሲያልፉ በተደጋጋሚ አስተውለናል።

በታላቁ መፅሐፍ መጽሐፈ አስቴር በምእራፍ 4 ቁጥር 13-14 አስቴር ስለምትባል አይሁዳዊት ሴት እንዲህ ተፅፏል *መርዶክዮስም አክራቲዮስን ሂድና ለአስቴር እንዲህ በላት አለው "አንቺ በንጉስ ቤት ስለሆንሁ ከአይሁድ ሁሉ ይልቅ እድናለሁ ብለሽ በልብሽ አታስቢ። በዚህ ጊዜ ቸል ብትይ እረፍትና መዳን ለአይሁድ ከሌላ ስፍራ ይሆንላቸዋል፣ አንቺና ያባትሽ ቤት ግን ትጠፋላችሁ፤ ደግምስ ወደ መንግስት የመጣሽው እንደዚህ ላለው ጊዜ እንደሆነ ማን ያውቃል?"* ይህን ጥቅስ ስመለከት ላለፉት 21 ዓመታት የሀገራችን ቀዳማዊት እመቤት የነበረቺው አዜብ ጎላ ትዝ ትለኛለች ትውልዷ የዛሬ ቅኝቴ ከሆነው ከወልቃይት ጸገዴ ህዝብ ነውና። አሳዛኝ ግጥምጥሞሽ።

የዘሩት ሜዳ ሙሉ የሚያምር ፍሬ ያንዠረገገ ሰብል ከነማሳው በጠራራ ጸሐይ የተዘረፉ፣ እልፍኝ ካዳራሽ ቤታቸው ከነ ሙሉ ንብረቱ በህዝብ ፊት የተነጠቁ፣ የቤት እንሰሶቻቸው ከነ አይነቱ እነዲሁም ልጆች ወልጄ ኩየ ድሬ እኖርበታለሁ ሃብት ንብረት አፍርቼ አከብሬና ተከብሬ ለልጅ ልጆቼ አወርሰዋለሁ ካሉት ቀዬና ሸንተረር በግፍ በጉልበት በሃይል ተዋርደውና ተጎሳቁለው እንዲሰደዱ የተደረጉ ምስኪን ህዝቦች፤ የወልቃይትና ፀገዴ ወገኖቻችን። ሴቶቻቸው በወያኔ ኢህ አዴግ በተደራጀና በተቀነባበረ መልኩ የራሳቸውን መሰል ወንዶች ሳይሆን አገዛዙ የመረጠላቸውን ወንዶች እንዲያገቡ ሆን ተብሎ የግፍ ግፍ የተሰራባቸው፤ ከስር ከመሰረቱ ነቅለው እንዲወጡና የአካባቢ፣ የመሬት ባለቤትነት እንዳያነሱ ተስፋ መሬታቸውን፣ ትዝታ ቀያቸውን የተወረሱ አሳዛኝ ህዝቦች፤ የወልቃይታ ፀገዴ ኢትዮጵያዊያን ወገኖቻችን። ታዲያ ይህ ይረሳል ወይስ ይለመዳል?

ከላይ እንዳየነው በታላቁ መፅሃፍ የተጠቀሰችው አስቴር አይገቡ ገብታ እና ንጉስ ባለቤቷን አሳምና የሞት ፍርድ የተፈረደባቸውን አይሁዳዊያን ወገኖቿን የቁርጥ ቀን ወገን ሁና ከሞት ስትታደጋቸው እናነባለን። ምስኪን የወልቃይትና የፀገዴ ህዝብ ግን ዘሩ ሲመከን፣ ሃብቱ ሲራቆት፣ ከቅየው በባዶ እጁ ሲባረርና ተመልሶ የይገባኛል ጥያቄ እንዳይጠይቅ ባገሩ ስደተኛና ለማኝ ሲሆን ወልዶ ያሳደጋትና የኔ የሚላት ቀዳማዊት እመቤት አዜብ መስፍን እንደ አይሁዳዊቷ አስቴር በቤተ መንግስት ብትሆንም ወገኖቿን ለመርዳት ግን ጊዜ አላገኘችም። ውሃ የተራጨችባቸው የወልቃይት ወንዞች፣ ጭቃ አቡኪታ የተሯሯጠችባቸው የፀገዴ ባድማዎች፣ አኩኩሉና ድብብዎሽ የተጫወተችባቸው የወልቃይት ፀገዴ ጫካዎች በግፍ ያለፍርድ ከታሪክ ምስክርነት ውጭ ወደ ታላቋ ትግራይ ሲካለልና ኗሪው ህዝብም አይሆኑ ሆኖ ሲባክን አዜብ ጎላ ግን ያለ ወገን የሚበላ፣ ያለ ዘመድ የሚደሰቱበት ያለ እህት ያለ ወንድም፣ ያለ አክስት ያለ አጎት የሚዝናኑበትን የቢዝነስ ኢምፓር እየገነባች ነበር። ታዲያ ይሄ እንዴት ይረሳል ወገን? እንዴትስ ይለመዳል?

ለወልቃይት ፀገዴ ህዝብ ተቆርቃሪና ደም መላሽ ወገን ከኛ ከኢትዮጵያዊያን ከወገኖቻቸው አለ። ጊዜው መቼም ይሁን መች ይህ በግፍ የተሰደደ ህዝብ ሃብቱን መሬቱን ሀገሩን ቅየውን ያገኛል። የተዋረደው ክብሩ የተንቋሸሸው ማንነቱ የተደፈረው እሱነቱ በወገኖቹ የማያቋርጥ ተጋድሎ ይመለሳል። ይህ ደግሞ አይቀርም። ወገኖቿ ሲሳደዱ ስትሳለቅ የነበረችው አዜብ ጎላ ግን የመከራ የስጋትና የጭንቀት ዘመኗ ጀምራል። ቤተመንግስቱን ለተመራጩ አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር ለማስረከብ ስታንገራግር የነበረውም ከዚሁ ፍርሃትና ጭንቀት የተነሳ እንደሆነ ይተወቃል። ምስኪን የወልቃይትና የጸገዴ ወገኖቻችን ባካል እንደተሳደዱ ሁሉ አዜብ ጎላ ዛሬ ኮሽታ የሚያስበረግጋት የራሷ ጥላ የሚያስደነብራት ድንጉጥና በመንፍስ ስደተኛ ሆናለች። በሰፈሩት ቁና መሰፈር ማለት ይህ ነው። ታዲያ ይህን ሁሉ የወገኖቻችንን ስቃይና መከራ ማን ይረሳል? እንዴትስ ተላምደን ልንኖር እንችላለን? ሁላችንም አንድ ሆነን የወያኔን ግብአተ መሬት ማፋጠን ይገባናል እንጂ።

---

## ኢቲቪ አሸባሪ !!! ኢቲቪ ሌባ !!!

. . . (ከገጽ 2 የዞረ)

ቢሆንም እንደምንም ብላችሁ ቆም ብላችሁ ነገን ለማየት ብትሞክሩ ለራሳችሁ እና ለልጆቻችሁ ይጠቅማችኋል።በየአቅጣጫው የሚነሳውን የህዝብ ድምጽ አፍነን እንዘልቃለን ብላችሁ ባትጃጃሉ መልካም የሚሆነው ለራሳችሁ ነው።

አሁንም ደግማችሁ አድምጡን የህዝቡ ጥያቄ አንድና አንድ ነው እርሱም የህግ የበላይነት ይከበር የሚል ነው።የህግን የበላይነት ለመቀበል አሻፈረኝ ብላችሁ በራሳችሁ ክፉ ስሜት ስትመሩ መኖራችሁ በህዝቡ ዘንድ ደህና ተደርጎ የሚታወቅ ነው። አመጻኝነታችሁ ጽዋውን ሞልቶ ተርፏል። ሃሳባችሁም ከህዝብ ጋር አብሮ የሚሄድ አልሆነም።ደግማችሁ ደጋግማችሁ በህዝቡ ላይ በደልን ፈጽማችኋል ኃጢአትንም አድርጋችኋል። የዚህ ሁሉ አመጽ ፍፃሜው ሞት እንጂ ህይወት አይሆናችሁም። ህወሃቶች የወገን ፍቅር ግድ አይላችሁም እንጂ ለህዝቡ ፍቅር እና ክብር ቢኖራችሁ ከታሰራችሁበት የአመጽ ሰንሰለት ራሳችሁን ለማስፈታት አሁንም እንዳልረፈደባችሁ ልናስታውሳችሁ እንወዳለን።በሃሰት ዜጎችን እየከሰሳችሁና በምናምንቴዎች እያስመሰከራችሁ የእድሜ ልክ እስራትና የሞት ፍርድ ማስፈርድን ብታቆሙ ይበልጥ ለእናንት ይበጃችኋል።

የግንቦት ሰባት ንቅናቄ የሙስሊም ኢትዮጵያዊያንን ጥያቄ ከልቡ ይደግፋል። ጥያቄው የህግ የበላይነት ጥያቄ ነው።ጥያቄው የፍትህ ጥያቄ ነው። ጥያቄው የአምልኮ ነፃነት ይከበር የሚል ጥያቄ ነው። እነዚህ ጥያቄዎች ዜጎች ዘረኞችን የሚለምኑት፤ ዘረኞች ህወሃቶች የሚሰጡትም ሊሆን አይገባውም።ሰው በመሆናችን ልንገለገልባቸው የሚገቡን አገርን እንደ አገር ሊያቆሙ የሚችሉ መሠረታዊ እሴቶች ናቸው።እንግዲህ በኢትዮጵያችን ፍትህ፤ነፃነት፤ እኩልነት፤ የህግ የበላይነት እና እውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ተገንብቶ እስኪታይ ድረስ በየፈርጁ የተጀመረው ትግል ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ነፃነታችንን ከማንም ለምንነን የምነቀበለው ምናምንቴ ነገር አይደለም። ዘረኛው ህወሃት የሚሰጠን ወይም ደግሞ የሚከለክለንም ሊሆን አይገባውም። ነፃነታችንንም ሰጥተን የምንቀበለው ሌላ ምንም ነገር የለም።

ግንቦት ሰባት ንቅናቄ በየፈረጁ እያካሄደ ያለውን የነፃነት ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል።ነፃነታችንን እስከምንቀደጅ ድረስ የሚከፈለውን መሥዋእትነት ለመክፈል ወደ ኋላ አንልም። እውነት ከእኛ ጋር ስላለችም እናሸንፋለን። ያን ግዜ ኢቲቭ የኢትዮጵያ ህዝብ ዓይንና ጆሮ ሆኖ ያገለግላል እንጂ ዘረኞችና ዘራፊዎች ህዝቡን ለማጥቃትና ለማሸማቀቅ አይገለገሉበትም። የነፃነት ጎህ ሲቀድም ኢቲቪ አሸባሪና ሌባ ከመባል ወጥቶ የህዝቡ አካል ይሆናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ !!!**

---

## የወያኔ የይስሙላ ፓርላማ ህገመንግስቱ ዉስጥ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ኢትዮጵያ ዉስጥ "የመልካም አስተዳደርና ሪፎርም ክላስተር" የሚባል ተቋም ወይም መዋቅር እንደሌለ ለማወቅ ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ እነዚሁ ዉስጥ አዋቂ ምንጮች በብዙዎች ሲጠበቅ በነበረዉ በብርሀነ ገ/ክርስቶስ ቦታ ቴዎድሮስ አድሀኖም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ መሾሙ ቴዎድሮስ አድሀኖም ከብርሀነ ገ/ክርስቶስ የተሻለ ድፕሎማት ሆኖ ሳይሆን ጉዳዩ "መተካካት" የሚሉት ወያኔ የፈጠረዉ አዲስ ፈሊጥ ነዉ ብለዋል። ይህ በእንዲህ እንዳለ አንድ ስማቸዉ እንዳይጠቀስ የፈለጉ ከፍተኛ የኦህዴድ ባለስልጣን እቺ "መተካካት" የሚሏት የመለስ ዜናዊ ፈሊጥ ለምን እስካሁን ድረስ በረከት ስምኦንን እንዳልነካችዉ ሊገባኝ አልቻለም ብለዋል። ወያኔ መተካካት ብሎ ስዩም መስፍንና ግርማ ብሩን ጨምሮ ብዙዎችን ከቦታ ቦታ ሲያዘዋዉር እስካሁን ድረስ ባለበት ቦታ የረጋዉና ያልተተካዉ በረከት ስምኦን ብቻ መሆኑን እኚሁ ከፍተኛ የኦህዴድ ባለስልጣን ተናግረዋል።

ሌላዉ ብዙዎችን ያናገረዉና ጉድ ያሰኘዉ የሰሞኑ ሹመት የይስሙላው ፓርላማ ምንም ዉይይት ሳያደርግበት እንደመጣለት ያጸደቀዉ የሁለቱ ተጨማሪ ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች ሹመት የአገሪቱን ህገመንግስት የጣሰ መሆኑ ነዉ። የኢትዮጵያ ህገመንግስት አንቀጽ 75 እዉቅና የሚሰጠዉ ለአንድ ጠ/ሚኒስትር ብቻ ሲሆን በዚሁ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ አንድ ላይ ጠ/ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ጠ/ሚኒስትሩ ተክቶት ይሰራል የሚል አረፍተነገር ተጽፏል፤ ስለዚህ በህገመንግስቱ መሰረት ኢትዮጵያ ዉስጥ መኖር ያለበት እስካሁንም የነበረዉ አንድ ምክትል ጠ/ሚኒስትር ብቻ ነዉ። አሁን በግልጽ እንደሚታየዉ ግን ከዚህ ቀደም የተሾመዉን ደመቀ መኮንንን ጨምሮ አገሪቱ ሦስት ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች ሊኖሯት ነዉ። ከአዲስ አበባ ዝግጅት ክፍላችን ድረስ ስልክ ደዉለዉ ያናገሩን አንድ የህግ ባለሙያ . . . የሰሞኑ የወያኔ የጅምላ ሹመት እጅግ በጣም የሚያስገርምም የሚያሳዝንም ነዉ ካሉ በኋላ በዚህ ሹመት መሰረት ጠ/ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ከሦስቱ ምክትል ጠ/ሚኒስትሮች ዬትኛዉ ነዉ ጠ/ሚኒስትሩን ተክቶ የሚሰራዉ የሚል ትልቅ ጥያቄ በመጠየቅ አስተያየታቸዉን ጨርሰዋል።

## ሀይለማርያም ደሳለኝ የራሱን ካቢኔ እንደማያዋቅር ተነገረ

የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ወደ ይስሙላ ጠቅላይ ሚንስትርነት የመጣው ሃይለማሪያም ደሳለኝ በይስሙላ ከተካበት ግዜ ጀምሮ ከዛሬ ነገ የራሱን ካቢኔ ይመሰርታል ተብሎ በጉጉት ሲጠበቅ ከአሁን በኋላ ሌላ ምርጫ እስኪደረግ ድረስ አዲስ ካቢኔ እንደማይመሰርት ለወያኔ ኢህአዴግ ማሳወቁን ለዝግጂት ክፍላችን ቅርበት ያላቸው ምንጮች ጠቆሙ:: አንደ ምንጮቹ አባባል ኃ/ማሪያም ደሰለኝ የራሱን ካቢኔ ማዋቀር ያልቻለዉ በይስሙላ ምርጫም ቢሆን አሸንፎ የመጣ አዲስ ጠ/ሚኒስትር ባለመሆኑ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏ። ኃለማርያም ደሳለኝ በመለስ ዜናዊ እግር የተተካ በመሆኑ አዲስ ካቢኔ ለፓርላማ አቅርቦ ማስጸደቅ አንደማይችል ቢነገርም እንደዚህ አይነቱን አሰራር በተመለከተ ህገመንግስቱ ላይ የተቀመጠ ምንም ነገር ስለሌለ ኃ/ማሪያም ደሰለኝ ካቢኔ ማቋቋም አይችልም የሚለዉ ህግ ህዝቡን በየቦታዉ ማወያየት ጀምሯል።

ኃይለማርያም ደሳለኝ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ በቆየባቸዉ ባለፉት ሦስት ወራት ለፓርላማዉ አቅርቦ ያስሾመዉ ሁለት ባለስልጣኖችን ብቻ ሲሆን አነሱም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመዉ የትምህርት ሚኒስትሩ ደመቀ መኮንንና ተጠባባቂ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር ሆኖ የተሾመዉ ብርሃነ ገ/ክርስቶስ ናቸዉ። በሌላ በኩል ደግሞ የሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትሩ ጁነዲን ሳዶ ባለቤቱ በሽብርተኝነት በመከሰሷና እሱን በተመለከተ ኦህዴድ ዉስጥ በተካሄደ ግምገማ የተነሳ ከሲቪል ሰርቪስ ሚኒስትርነቱ ይነሳል ተብሎ እየተጠበቀ ቢሆንም መቼ ይነሳል ማንስ ይተካዋል የሚሉት ጥያቄዎች ግን እስካሁን ድረስ መልስ የተገኘላቸዉ አይመስልም።

## ግፈኛው የወያኔ አገዛዝ በመላ አገሪቱ ሙስሊሞችን እያስገደደ ለተቃውሞ ሰልፍ ሊያስወጣ መሆኑ ተሰማ

ከወያኔ ኢህአዴግ የተገኙ ምንጮችን በመጥቀስ የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደገለጸው በአገሪቱ ውስጥ በሚገኙና ዘረኛው አገዛዝ በሙስሊሙ ላይ በሚፈጽመው ኢሰብአዊ ድርጊት የተነሳ ተቃውሞ ያሰነሳሉ በተባሉ አካባቢዎች በሙሉ ፣ የአገዛዙን አቋም የሚደግፉ አስገዳጅ ሰልፎች እንደሚደረጉ ታውቋል።

አብዛኛው ሙስሊም ህዝብ ተገዶ እንዲወጣ፣ የወያኔ ኢሃዴግ ድርጅት አባላት ከፍተኛ ተልእኮ እንደተሰጣቸው ለማወቅ ተችሎአል። በትናንትናው እለትም በቅርቡ የመንግስት ታጣቂዎች 4 ሰዎችን በገደሉበት ገርባ እና ደጋን ወያኔን የሚደግፉ አስገዳጅ ሰልፎች መደረጋቸውን ኢሳት አክሎ ገልጿል።

የሰልፉ ዋና አላማ በፍርድ ሂደት ላይ የሚገኙት የድምጻችን ይሰማ የሙስሊም ኮሚቴ አባላት አሸባሪዎች ናቸው የሚል መልእክት ለማስተላለፍ እንደሆነም የተገኘው መረጃ ያመለክታል ብሏል ኢሳት። ወያኔ ኢህአዴግ በኮሚቴ አባላቱ ላይ ለፍርድ ቤቱ ጠንካራ ማስረጃ ማቅረብ ባለመቻሉ በዳኞች ላይ ተጽኖ ለመፍጠር ማሰቡን የደረሰን መረጃ ያመለክታል ሲል ኢሳት ዘገባውን አጠቃሏል።

## በሀብታሞች መኪና የሚጨናነቁ የአዲስ አበባ መንገዶች እግረኞችን መሄጃ ማሳጣታቸዉ ታወቀ

በስራ እጦትና አገሪቱ ዉስጥ በተፈጠረዉ ከፍተኛ የኑሮ ዉድነት የተነሳ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ዜጎች የሚላስና የሚቀመስ አጥተዉ በሚሰቃዩባት አዲስ አበባ ዉስጥ አዉሮፓና አሜሪካ ዉስጥ እንኳን በብዛት የማይታዩ ዉድና ዘመናዊ መኪናዎች መንገዶችን እያጣበቡና እግረኛዉን መድረሻ እያሳጡ መሆኑ ታወቀ። ፌራሪ፤ ሀመር፤ ቤንትሊና ፖርሻን የመሳሰሉ እጅግ በጣም ዉድ የሆኑ መኪናዎች አንዴት አገር ዉስጥ አንደሚገቡና ማን እንደሚዛቸዉ ባይታወቅም እነዚህ መኪናዎች አዲስ አበባ ዉስጥ በብዛት እንደሚታዩና የእነዚህ የተሽከርካሪዎች ብዛት ከህዝቡ የመግዛት አቅም በላይ እያደገ መሆኑ እየተነገረ ነዉ።

ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ እነዚህን ዘመናዊ መኪናዎች ማነዉ የሚገዛቸዉ ብሎ የጠየቀዉ አንድ የዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ተማሪ ጥያቄዉን ሲመልስ ወያኔና ወያኔን ከተጠጉ ሙሰኛ ዜጎችና አገር ሲወረር አብረህ ውረር በሚል ፈሊጥ ከተለከፉ ጥቂት ግላሰቦች ዉጭ እነዚህን መኪናዎች እንኳን ሊገዙ መኪናዎቹ መኖራቸዉን የሚያዉቁ ዜጎች ቁጥር እጅግ በጣም ትንሽ ነዉ ብሏል። ወጣቱ ተማሪ ንግግሩን በመቀጠል ኢትዮጵያ የዕንቆቅልሽ አገር ሆናለች፤ደሃዉ ምን በልቶ አንደሚኖር አይታወቅም ሀብታሙም ገንዘቡን ከዬት እንደሚያመጣዉ ብዙ የሚታወቅ ነገር የለም፤ ሀብታሙ ይዘርፋል ደሃዉ አምላኩን ለምኖ ያድራል ብሏል።

በሌላ በኩል ደግሞ የአዲስ አበባ መንገዶች ግንባታና ጥገና ስራ እጅግ በጣም ብዙ ግዜ እየወሰደ በመሆኑ አዲስ አበባ ዉስጥ በየቦታዉ ከፍተኛ የመንገድ ላይ መጨናነቅ እንደሚታይ ለማወቅ ተችሏል። ለምሳሌ ከላምበረት ወደ መገናኛ የሚወስደዉ የሦስት ኪሎ ሜትር አስፋልት መንገድ ሥራ በተጀመረ በሁለተኛ ዓመቱ የቁፋሮዉ ስራ አሁንም አልተጠናቀቀም። ከዚህ በተጨማሪ ገንዘብ ከመሰብሰብ ዉጭ የአገር ፍቅርና የሥራ ፍቅር በመጥፋቱ የብዙዎቹ የሥራ ኃላፊዎች ዘመዳቸው ሙስናና ገንዘብ ብቻ ነው ሲሉ ብዙዎች ትችት በመሰንዘር ላይ ናቸዉ።

## ኢትዮጵያ ዉስጥ ህጎችና ፖሊሲዎች በወረቀት ላይ የሚሰፍሩ እንጂ የማይተገበሩ መሆናቸውን ሪፖርተር አጋለጠ

የወያኔ ስርዓት ከሚመጣው ህዝባዊ ቁጣ ራሱን እንዲከላከል በሚያወጣቸው ተከታታይ ጽሁፎች እያስጠነቀቀ ያለው ሪፖርተር ባወጣው በዚህ ጽሁፍ ፍርድ ቤቶች ራሳቸውን የቻሉ ነጻ የህግ ተርጓሚ አካላት እንደሆኑ በወረቀት ላይ የሰፈረ ቢሆ ንም በተግባር ግን ፍትህ ዘወትር እየተረገጠ የሚውልባት፣ጉቦ የአንቀጾች ሁሉ የበላይ አንቀጽ የሆነባት፣ በአቅመ ደካሞች የምትመራ ሀገር ናት - የወያኔዋ ኢትዮጵያ በማለት አብራርቷል።

በማያያዝም የፍትህ መጓደል አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል፣የፍትህ አካላት የአቅምም የአመለካከትም ችግር አለባቸው፤ በመሆኑም የስነ ምግባር ጉድለትና የብቃት ችግር የወያኔዋ ኢትዮጵያ ዳኞች፣አቃቢያን ህግና ጠበቆች ዓይነተኛ መገለጫዎች ናቸው ብሏል። ስለ መልካም አስተዳደር እየተለፈፈ ቢውልም በተግባር ግን አቤት ብዬ ሰሚ አገኘሁ፣ ቅሬታ አቅርቤ ይፈታልኛል የሚል ዜጋ የለም በማለት የህዝቡ ብሶት ጣራ የነካ መሆኑን አመላክቷል።

ዛሬ ዛሬ በኢትዮጵያ ኢንቨስት ለማድረግ እቅድ ማውጣትና ለተግባራዊነቱ መንቀሳቀስ ፈጽሞ አይቻልም ያለው ጋዜጣው ይልቁንም " ሰው ያመለክታል ሃላፊ ይፈጽማል " መሆኑ ቀርቶ " ሰው ያስባል እግዜር ይፈጽማል " በሚል ሁሉም ነገር ለፈጣሪ የተተወበት ሁኔታ ነው ያለው ሲል ገልጿል።

ሌላው ዋነኛ የስርዓቱ ባህሪ " ሰው እንደ ማንነቱና እንደ ገንዘቡ ይስተናገዳል " የሚል መሆኑን ገልጾ እውነታው ከዚህም የከፋ፣ ከዚህም የመረረ መሆኑን ሲያብራራ ህዝብ የበደለ ፣ የሃገር ሃብት የዘረፈና ህግ የረገጠ የሚሸምበት፣ ተጠያቂ መሆን ያለበት ጠያቂ የሚሆንበት ስርዓት ነው የወያኔ ስርዓት እናም ይሄ

አደጋ አመላካች በመሆኑ ስርዓቱ አይቀሬ ሞቱን ማራዘም ከፈለገ በአስቸኳይ የእርምት ርምጃ መውሰድ እንዳለበት አሳስቧል።

## ህወሀት ዉስጥ በተፈጠረዉ አለመግባባት የተነሳ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ባለፉት አራት ወራት አልፎ አልፎ የተወሰኑ አንዳንድ ጉዳዮች ቢኖሩም ዉሳኔዎቹ ፓርቲዉን ለሁለትና ለሦስት በመከፋፈላቸዉ አንዱም ዉሳኔ ተግባራዊ ሆኖ አያዉቅም።

የአየር ሀይሉ አዛዥ የሜጀር ጄነራል ሞላ ሀይለማሪያም በሜጀር ጄነራል መሀሪ ዘውዴ መተካትና አሁን በቅርቡ ደግሞ ተመልሶ የቀድሞ ቦታዉን መያዝ የሚያሳየዉ ህወሀቶች ምን ያህል እንደተከፋፈሉና ደካማ እንደሆኑ ነዉ ሲሉ በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ይስማማሉ። አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ሲናገሩ እዚህ ላይ አንድ የሚገረም ነገር ቢኖር በስግብግብ ጓደኞቹ አለመግባባት የተነሳ አዲስ የተሰጠዉ ስልጣን ባይበረክትለትም ጄኔራል ሞላ ሀይለ ማሪያምን የተካዉ ሜጀር ጄነራል መሀሪ ዘዉዴ ሲሆን ሁለቱም ጄኔራሎች ህወሀትን ለረጂም ግዜ ያገለገሉ ነባር ታጋዮች መሆናቸው ነው ብለዋል። ዛሬ ህወሀትን ቀረብ ብሎ የተመለከተ ሰዉ የሚያስተዉለዉ ነገር ቢኖር ህወሀት መሪ የሌለዉ ፓርቲ መሆኑንና በአባላቱ ዉስጥ የሚታየዉ በአዉራጃ የመከፋፈል ስሜት እየጎላ መምጣቱን ነዉ በማለት አስተያየት ሰጪው አክለው ተናግረዋል።

## ዘረኛዉ የወያኔ ዘገዛዝ የአዲስ አበባን 125ኛ አመት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ልደት አከባበርና የኩማ ደመቅሳን ንግግር በማንሳት ያናገርናቸዉ አንድ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የታሪክ ምሁር እንደተናገሩት ኩማ ደመቅሳ “ጀሮ ለባለቤቱ ባዳ ነዉ” የሚሉት ተረት ሆኖበት ነዉ አንጂ በ125 አመት የአዲስ አበባ ከተማ ታሪክ ዉስጥ መብራትና ዉሃ በአራት ቀን አንዴ ለህዝብ ሲታደል ያየነዉ በወያኔ ዘመን ብቻ ነዉ ብለዋል። ምሁሩ ንግግራቸዉን በመቀጠል የአዲስ አበባ ከተማ የመብራት ችግር የወያኔን እድሜ ያክል የቆየ ችግር ሲሆን ባለፉት ሁለትና ሦስት አመታት ደግሞ ከተማዋ ታይቶ የማይታወቅ የዉሃ እጥረት ችግር ዉስጥ ተዘፍቃለች ብለዋል። ምሁሩ የራሳቸዉን ቤት እንደ ምሳሌ ወስደዉ እንደተናገሩት እሳቸዉ ወደሚኖሩበት ሠፈር ዉሃ የሚመጣዉ በአራት ቀን አንዴ ስለሆነ ለአራት ልጆቻቸዉ የሚጠጣ ዉሃ ለማምጣት በየሳምንቱ ከአዲስ አበባ እንደሚወጡ ተናግረዋል።

ሌላዉ የወያኔ ተላላኪና የዕለቱ ተናጋሪ የነበረዉ ደመቀ መኮንን ደግሞ አዲስ አበባ የዓለም አቀፍና የአፍሪካ መዲና ሆና የወጣችው ካለፉት ሁለት አሥርተ ዓመታት ወዲህ ነው በማለት የእድሜ ልክ የወያኔ ታማኝ ሎሌ መሆኑን በተግባር አረጋግጧል። ደመቀ መኮንንም ሆነ ጌቶቹ የወያኔ ባለስልጣኖች ያሻቸዉን ይለፈልፋሉ እንጂ አዲስ አበባ መቼና በማን ዘመነ መንግስት የአፍሪካ መዲና እንደሆነች የኢትዮጵያ ህዝብ በሚገባ ያዉቃል ያሉን አንድ የአዲስ አበባ ነዋሪ የወያኔ ተልዕኮ የአገራችንን ታሪክ ማጥፋት ብቻ ሳይሆን ታሪክ መቀማትም ነዉ ብላዋል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**መካከኛ ሞገድ:-** በ 358 MB, በ 837 kHz

**አጭር ሞገድ:-** በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2:30 እስከ 3:00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 እስከ 3:30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11:30 እስከ 12:00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታሳውቁን እንገልጻለን።

ማሳሰቢያ:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org